# ሕገ ወጥ ድርጊት ተፈጸመብኝ የሚል ከሕገ ወጦች ጋር አያብርም

ታምራት ታረቀኝ

አቶ ስየ አብርሀ መጽሀፍ ጻፉ ሲባል ለማግኘት ገጉት ያደረብኛ ከደደቢት እስከ ምኒልክ ቤተ መንግስት በነበረው ጉዞ አበይት የሆኑትን ይልቁንም ሌላው ተራ ታጋይ ሊያውቃቸው የማይችላቸውን ግን ትውልድ ሊያውቃቸው ታሪክም ሊመዘግባቸው የሚገቡ ጉዳዮችን ይተርኩልናል በሚል ስሜት ነበር፡፡ ይህም ቢቀር ለርሳቸውና ለአቶ መለስ መለያየት ምክንያት ብለው የሚጠቅሱትና ከ700 ሺህ በላይ ወገኖቻችንን እንደበላ የሚነገርለት የኢትዮ ኤርትራን ጦርነት ስረ ምክንያት ይነግሩናል፡ ኤርትራ የግል ኢትዮጵያ የጋራ ሆነው የነበረበትንም ምስጢር ያጫውቱናል፡ ለጦርነቱ መቀስቀስ የነበረውን ድርሻም ያሳዩናል ወዘተ የሚል እምነትም ነበረኝ፡፡

« በህውኃት ውስጥ ለተከሰተው መሰነጣጠቅ ዋናው መንስዔ በኢትዮ ኤርትራ ጦርነት ዙሪያ የተነሳው ልዩነት ነበር» በማለት በክፍል አንድ ጀምሮ እስከ ገጽ 440 የሚዘልቀው መጽሀፍ አባሪዎቹ ሲነሱለት ገጽ 249 ላይ «....በአገራችን የታወቀ ተመርጦ የተቀመጠ ስታንዳርድ ያሟሉ እስር ቤቶች ሊኖሩ ይገባል፡፡» ብሎ ነው የሚያበቃው፡፡

አቶ ስዬ ከህውኃት የተባረርኩት በህገ ውጥ ሁኔታ ነው ያሉበትን በመጠኑ ያሳዩበትና የሙስና ሰበብ ተፈጥሮ ከነቤተሰባቸው ለእስር የተዳረገበትን ሁኔታና የክሱን እንዴትነት የገለጹበት ይህ መጽሀፍ የያዘው ትረከ ቀደም ብሎ በተለያየ መንገድ ከምናውቀው በላይ የደረሰባቸውን ግፍ የሚያሳይ በመሆኑ የተፈጸመው ድርጊት ልብ ይነካል፡፡

ድርጊቱ የተፈፀመው አብረው ድንጋይ ተንተርሰው እያደሩ ወደ አኪር እየበሉ በጫካና በየገደሉ እየኖሩ ከምንም በላይ ደግሞ የወገንን ደም( ከደርግም ከህውኃትም ወገን የተሰለፈው ወገን ነው) በጋራ እየተረማመዱ ለሥልጣን በበቁ የትግል ጓዶቻቸውና አብረው በፈጠሩት ሥርዓት መሆኑ የአቶ ስየን ህመም የሚያበረታው ይሆናል፡፡

አቶ ስዬ የዘረዘሩት ማንም መጽሀፉን ያነበበን ሰው ልብ የሚነካ ድርጊት የተፈጸመባቸው ከአቶ መለስ ጋር በመጣላታቸው እንደሆነ ገልጸዋል፡፡ አቶ መለስንም ባላጋራዬ እያሉ ነው ብዙ ቦታ የጠቀሱዋቸው፡፡ነገር ግን ለዚህ ሁሉ ያበቃ ልዩነት በአንድ ጀንበር የተፈጠረ ነው፡ ወይንም እንደተባለው የኢትዮ ኤርትሪያ ጦርነት የወለደው ነው ብሎ ለማመን ይቸግራል፡፡ ውስጥ ለውስጥ ሲብላላ ለቆየ ልዩነት መፈንዳት ምክንያት ሆኖ ካልሆነ በስተቀር፡፡ አቶ ስዬ ግን ይህን ሊያሳዩን አልቻሉም፡፡ « በሕገ ወጥ መንገድ ያባረራቸው» ህውኃትም ይሁን ኢህአዴግ አብረው ያደራጁት ነው፡፡ ባልሰራነው ስራ ወንጀል ፈጥረው ከሰሱን ያሉዋቸው፡ ፍርድ ቤት የፈቀደላቸውን ዋስትና ከልክለው ይልቁንም ከመንገድ አፍነው መልሰው እስር ቤት አስገቡኝ ያሉዋቸው የትግልም የሥልጣንም « ጓዶቻቸው» ናቸው፡፡ የሀሰት ምስክር አደራጁ፡ ሰዎች በእኛ ላይ እንዲመሰክሩ ማግባባትም መደለልም ፈጸሙ ወዘተ ያሉዋቸው የፍትህ ሥርአቱ አካላትም በርሳቸው አብሮነት የተደራጁ ናቸው፡፡ ርሳቸው በሥልጣን ላይ በነበሩበት ወቅትም ተመሳሳይ ድርጊት በሌሎች ዜጎች ላይ ሲፈጽሙ የነበሩ ናቸው፡፡ ስለሆነም በተቋማትም ሆነ በግለሰቦች ለተፈጸመው አቶ ስየ የኃላፊነት ድርሻ ሊወስዱ ይገባ ነበር፡፡ ርሳቸው ግን ለሁሉም ነገር አቶ መለስን ተጠያቂ ማድረግን ነው የመረጡት፡፡

በሌሎች ላይ ሲደርስ የነበረውንና በእኔም ላይ የደረሰውን ከእኔም በኃላ በተለያየ ግዜ በሌሎች ዜጎች ላይ የደረሰውን ህገ ወጥ ተግባር የፈጸሙ ተቋማት በዚህ አቋምና ይዞታ እንዲደራጁ በማድረጉ ሂደት እኔም ዋንኛ ባለድርሻ ነበርኩ ማለት ከአቶ ስዬ ይጠበቅ ነበር፡፡ እንደውም ቢችሉና ቢደፍሩ እነዚህ ተቋማት ሌላው ቀርቶ ርሳቸው ደረሰብኝ ያሉትን ህገ ወጥ ተግባር ለመፈጸም ያበቃቸው አደረጃጀት እንዴት ለምንና በማን እንደተከናወነ ሊነግሩን በተገባ ነበር፡፡ ርሳቸውን ከምኒልክ አደባባይ በመኪና ጠልፎ ለመውሰድ የደፈረ ተቋም በሌሎች ዜጎች ላይ ምን ሊያደርስ እንደሚችል ይህንንም ድፍረት ከወዴት እንዳገኘው ከርሳቸው በላይ ሊያውቅ የሚችል የለምና በጥቂቱም ቢሆን ማሳየት ቢችሉ መጽሀፋቸውን የተሻለ ያደርገው ነበር፡፡

ስዬ ትናንት የተባረሩበትና ዛሬ «ሊቀመንበር»ነኝ የሚሉበት ፓርቲዎች ተመሳሳይ ድርጊት::

ከአቶ ስዬ መጽሀፍ በመነሳት ብዙ ጥያቄዎችን ማንሳት አስተያየቶችንም መሰንዘር ይቻላል:: ነገር ግን ነገሮችን እየከፋፈሉ ደረጃ በደረጃ ከላቀረቡዋቸው በመረዘም አንባቢን ያሰለቻሉ:አንዱ ጉዳይ በሌላኛው እየተዋጠ ተገቢውን ትኩረትም ሳያገኝ ይቀራል:: እኔም አስተያየቴን መጽሀፉ በጀመረበት የኢትዮ ኤርትራ ጦርነት ዙሪያ ለመጀመር ሳውጠነጥን ብዙም ሳይጓዙ ገጽ 35 ምዕራፍ ሁለት ላይ « የአቶ መለስ ቡድን በሕግ ፊንታ የኃይል መንገድ መምረጡ » በሚል ርእስ ያቀረቡት ትረካ ስለሳበኝ ከዚሁ መጀመር መረጥሁ::
ርሳቸው የአቶ መለስ ቡድን ፈጸመው የሚሉት ተግባር እኛ የኢ/ር ግዛቸው ቡድን ፈጸመው ከምንለው ተግባር ጋር ተመሳሳይ ነው:: የድርጊቱ መመሳሰል ሁላችንም የወጣነው ከዚህችው መሬት በመሆኑ ነው ሊባል ይችል ይሆናል:: አቶ ስዬ በራሳቸው ተፈጽሞ ያወገዙት ድርጊት በሌሎች ላይ እንዲፈጸም ከኳላ ሆነው የመግፋታቸው የዛው ፓርቲ አባል በመሆንም ሕገ ወጥ ተግባር ከፈጸሙ ሰዎች ጋር ማበራቸው ከዚህ አልፈውም ሕገ ወጥ ተግባር የተፈጸመባቸውን ሰዎች አውጋዥ ሆነው መሰለፋቸው ግን አንቆቅልሽ ነው:: ጉዳዩን ይበልጥ አንቆቅልሽ የሚያደርገው ደግሞ ድርጊታቸው ከራሳቸውም ንግግር ( ጽሁፍ) ጋር የሚቃረን መሆኑ ነው:: ከጽሁፉ ተመርጠው ከመጽሀፉ ጀርባ ላይ ከሰፉሩት አንዱ እንዲህ ይነበባል:: «ሌላ ሲበደል እኔን ካልነካኝ የራሱ ጉዳይ: ምን አገባኝ ማለትን መተው ይኖርብናል:: ምክንያቱም ያንድ ዜጋ መብት ዛሬ ሲገፈፍ ከእያንዳንዳችን መብትና ክብር ትንሽ እየተቆረሰ እየተጣለ መሆኑን ልንገነዘብ ይገባል:: ይህ ተሰምቶን በሌሎች ወገኖቻችን ላይ የሚደርሰውን በደል ለማስቆም በጋራ መቆምን መልመድ ይገባናል:: በሌሎች ላይ የሚደርሰው የመብት ጥሰት እኛንም ሳይቆነጥጠን ዝም ካልን የግዜ ጉዳይ ካልሆነ በስተቀር ከእያንዳንዳችን ቤት ዘንድ መምጣቱ አይቀርም ::»
ለአቶ ስዬ በደል ማለት መንግሥታዊ ሥልጣን ላይ ባሉ ዜጎች ብቻ የሚፈጸም ካልሆነ በስተቀር ድርጊታቸው በዚህ አንቀጽ ከተገለጸው ሀሳባቸው ጋር አይስማማም:: ፓርቲያቸው በነበረው ህውኃት ተፈጸመብኝ የሚሉት ለርሳቸው በደል ከሆነ አንድነት ፓርቲያችንን ለመቆጣጠር ግዜና እድል በፈቀደላቸው ጥቂት ሰዎች ተፈጸመብን የምንለው ለእኛ በደል የማይሆንበት ምክንያት የለም::
አንድነት ውስጥ የሆነውን አቶ ስየ ካስነበቡን ጋር ስናስተያየው በብዙ መልኩ ተመሳሳይነት አለው:: የመመሳሰሉ ምስጢር አቶ ስዬ ወደ ፓርቲው ከመግባታቸው በፊት ከጀርባ ሆነው ስላቀነባበሩት ነው እንዳይባል በራሳቸው ደርሶ ሕገ ወጥ ብለው ያወገዙትንና በደል ያሉትን ድርጊት በሌሎች ላይ እንደምን ይፈጽማሉ የሚል የህሊና ሙግት ይገጥመናል::
በአንድ ግዜ ከህውኃት የተባረሩት የማእከላዊ ምክር ቤት አባላት ቁጥር 12 ነው::ከአንድነት ደግሞ 11:ይህን አንድ ብለን ከሚመሳሰሉት ድርጊቶች ጥቂቶቹን እንይ::
☛« በሕውሀት ማእከላዊ ኮሚቴ የተፈጠረው የሀሳብ ልዩነት ለወራት ስብሰባ ተቀምጦም የሚፈታ አልሆነም::መጨረሻ ሃሳብን በሃሳብ ማሸነፍ መሆኑ ቀረና ድምጽን በማስፈራራትና በልመና የመግዛቱን ዘመቻ አቶ መለስና ስብሀት ተያያዙት::»( ገጽ 35)
አንድነት ውስጥ ለወራት ስብሰባ መቀመጥ የማይታሰብም የማይቻልም ነው:: ምክር ቤቱ ሲገናኝ ግን በተለይ ወደ ኃላ ላይ የሚቀርቡለት አጀንዳዎች በአንድ ቀን ውይይት አልቋጭ እያሉ ሁለት ተከታታይ ቀናት ይሰበሰብ ነበር:: በእነ ፕ/ር መስፍን የቀረበለትን ጽሁፍ መነሻ አድርጎ የፓርቲውን አንቅስቃሴ ቃኝቶ የውሳኔ ሀሳብ እንዲያመጣ ኮሚቴ አቋቁሞ ም/ቤቱ ጽሁፉንና ሪፖርቱን ጉን ለጎን እየመረመረ ያሳላፋቸው 22 ውሳኔዎች ለእነ ኢ/ር ግዛቸው ቡድን ስላልጣመው ውሳኔዎቹን ተፈጻሚ ላለማድረግም ሆነ በቀጣይ ተመሳሳይ ውሳኔ እንዳይተላለፍ የመረጠው መንገድ የምክር ቤት አባላትን በተለያየ መንገድ መደለልና መያዝን ነበር:: በተለይም በምርጫ 2002 ዕጩነት:: ይህም በመሆኑ የፓርቲው ፕርግራም በሶስት ሰዎች ሲለወጥ ዝም ብሎ የሚያይ ምክር ቤት እስከ መሆን ደረሰ::
☛« ከማእከላዊ ኮሚቴ ቀጥሎ ያለው ህጋዊ መድረክ የድርጅቱ ጉባዔ እንደመሆኑ ማእከላዊ ኮሚቴ መቋጫ ሊያደርግለት ያልቻለን ጉዳይ ወደ ድርጅቱ ጉባዔ ቀርቦ ጉዳዩ እልባት ያግኝ ማለታችንን እንደ ትልቅ ጉዳይ አድርጎ አቶ መለስ በህገ ደንቡ ምንም ቦታ የሌለውን የካድሬ ስብሰባ መቀሌ ላይ በመጥራት ዲሞክራሲያዊ ማእከላዊነትን ጥሰዋል: ስብሰባ ረግጠዋል: ብሎ ባደረገው ቅስቀሳ ከድሬዎቹ እኛን እንዲያወግዙ አድርጓል.::» (ገጽ 36)
የአንድነት ም/ቤት 22ት ውሳኔዎች በተላለፉ እለት ስራ አስፈጻሚው እነዚህን ውሳኔዎች በተቀመጠላቸው የግዜ ገደብ ውስጥ ተግባራዊ የማያደርግ ከሆነ ቀጣዩ ርምጃ ጠቅላላ ጉባዔ

*መጥራት ይሆናል በሚል ከአንድ አባል ሀሳብ ሲቀርብ « ይህን ሀሳብ ስሰማ በጣም ነው የደነገጥኩት በአሁኑ ሰዐት ጠቅላላ ጉባዔ እንዴት ይታሰባል » በማለት ፈጥነው የተቃወሙት ዋና ጸኃፊ የነበሩት አቶ አስራት ጣሴ ናቸው። ችግሮች በውይይት እንዳይፈቱም « ከማንም ጋር አንወያይም የፖለቲካ ውሳኔ እንወስናለን » በማለት የውይይትን በር ጥርቅም አድርገው የዘጉት እኚሁ ሰው ናቸው። እኛ ግን ችግሮችን ማሳየታችን በውይይት እንፍታውም ብለን መጠየቃችን ወንጀል ሆኖ በሀገር ውስጥም በውጪም ለሚገኙ አባላትና ደጋፊዎች « ሰርጎ ገብ አለባቸው፡ ምስጢር የሚያወጣ አለባቸው፡ አንድነትን ለማፍረስ የሚንቀሳቀሱ ናቸው ባዕድ አካል ውስጣችን ገብቷል ወዘተ» የሚል አሉባልታ ተነዛብን። አሉባልታው ሀሰት መሆኑ ለሁሉም አባላት ዘግይቶ ግልጽ ቢሆንም በወቅቱ አምነው የተቀበሉ ግን እኛን ለማወገዝ በቅተው ነበር።*

*☛« ህውኃት የሚመራበትና አብዛኛውን ድምጽ ያገኘ ሀሳብ ተግባራዊ ይሆናል የሚለው የዴሞክራሲያዊ ማእከላዊነት መርህ የብዙሀኑን ሀሳብ በማራመዱ ዲሞክራሲዊ ሊሰኝ ቢችልም በተለይ ከውህዳኑ አንጻር ለዲሞክራሲ ትልቅ እንቅፋት ነው፡ የውህዳኑን ነጻነትና ስብእና ይጋፋል።» (ገጽ 39)*

*አንድነት ውስጥ በአብልጫ ድምጽ ተወስኖ እኛ አንቀበልም ተፈጻሚ መሆንም የለበትም ያልነው ጉዳይ የለም። የአመራር ቡድኑ ግን ለፕሮፓጋንዳ ይጠቅመኛል ብሎ በማሰብ « በአብልጫ ድምጽ የተሸነፉበትን ውሳኔ አንቀበልም ብለው ነው» ይል ነበር። ምን የሚል ውሳኔ ብሎ የጠየቀው ግን የለም፡ እኛን ለአብልጫ ድምጽ የማይገዙ ብሎ ማውገዝ አንጂ። የሌላው አልገረመኝም አቶ ስዬ በብዙሀን ውሳኔ የተባረርን መሆናችንን መናገራቸውና በአንድነት ጉዳይ ምንም አንደማያገባን ገልጸው ፖሊስ እንዲያስረንም አመልክተው የፖሊስ ትብብር ያለማግኘታቸውና እኛ ያልታሰርነው የመንግስት ድጋፍ ስላለን አንደሆነ አድርገው በአንድ ጋዜጣዊ መግለጫ ላይ ያውም በንዴት መናገራቸው መጽሀፋቸውን ካነበብኩ በኃላ ሳስበው ይበልጥ አስገርሞኛል።*

*☛« በጦር ሜዳ የአዛዥን ትዕዛዝ አልቀበልም ማለት ወንጀል ነው። ማንም ይሁን ምን የበላይህን ትእዛዝ አክብር ፡ፈጽም፡ ከፈጸምክ በኋላ ግን ጥያቄህን ማቅረብ ትችላልህ ነው የሚለው። በፖለቲካዊ ድርጅት ግን መመሪያ ሲሰጥህ ከመርህ አኳያ ከሕግ አኳያ ወይም ከህሊና ፈርድ አኳያ ትክክል አይደለም ብሎ መቃወም ወንጀል ሊሆን ባልተገባ ነበር። በሕውኃት የነበረው ሁኔታ ግን ከወታደር ቤቱ ግዳጅም የባሰ ነበር።»*

*አንድነት ውስጥ ከሊቀመንበራችን ወ/ት ብርቱካን ሚደቅሳ እስር ጋር በተያያዘ አመራሩ በያዘው አቋም ላይ ጥያቄ አነሳን፡ « የብርቱካን ወንበር ጠባቂዎች» ከሚል ፍረጃ አልፎ « የብርቱካንን ፎቶ በማስቀደም ፓርቲ ለማፍረስ የሚንቀሳቀሱ» ተብለን ተወነጀልን። አንድነት ከመድረክ ጋር ለመቀላቀል የጀመረው መንገድ የፓርቲውን ፕሮግራም ያላከበረ መተዳደሪያ ደንቡንም ያልጠበቀ ነውና ጥድፊያው ረገብ ይበልና እንወያይበት ብለን በመጠያቃችን ጸረ ትብብር ተደርገን ተፈረጅን በአፍራሽነትም ተወነጀልን። በፖለቲካ ሂደት ውስጥ መጠየቅ ወንጃል ያለመሆኑን በመጽሀፋቸው የሚነግሩን አቶ ስየ ግን እኛን ወንጃይ ሆኑ።*

*አቶ ስየ ከአቶ ስብሀት ጋር ሲነጋገሩ የተባሉትን ሲገልጹ «ችግሩ እንዲፈታ ፍልጎት ካላችሁማ የሰራችሁትን ጥፋት አምናችሁ ግለ ሂስ አድርጋችሁ ወደ ማእከላዊ ኮሜቴ መመለስ ነው አለኝ፡» ብለዋል። (ገጽ 78)*

*የአንድነት ችግር ያሳሰባቸው ወገኖች ችግሩ ለምን በውይይት አይፈታም በማለት ለማደራደር በማሰብ ጥያቄ ሲያቀርቡ ከእነ ኢ/ር ግዛቸው የሚሰጠው ምላሽ « ይቅርታ ጠይቀው ወደ ፓርቲው መመለስ ይችላሉ » የሚል ነበር። አንደ እነ አቶ ስየ ወደ ማእከላዊ ምክር ቤት አንኳ አይደለም። ርሳቸው ለአቶ ስብሀት ሰጠሁት የሚሉትን መልስ ያነበበ ማንም ሰው አቶ ስየ የእነ ኢ/ር ግዛቸውን « ይቅርታ ይጠይቁ» ጥያቄ በመደገፋቸው መገረሙ አይቀርም።*

*« በሌላ አነጋገር ስብሀት ተማረክ እጅህን ስጥ ነበር እያለኝ፡ የነበረው፡ እኔ ግን በሀሳቡ አልተናደድኩም። ከት ብዬ ሳቅሁበትና ስማ ስብሀት የእኔን ወንድነትና ሱሪ ትጠራጠራለህ እንዴ? በማለት ጠየቅሁት» በማለት ነው ለአቶ ስብሀት ነጋ የሰጡትን መልስ የሚነገሩን። (ገጽ 79) አቶ ስየ እነ ኢ/ር ግዛቸው ለእኛ ያቀረቡትን ይቅርታ ይጠይቁ ጥያቄ ሲደግፉ የእኛን ሱሪ በመጠራጠር ይሆን?*

አቶ ስዬ ምን አይተው አንድነት ገቡ

*«ለገዛ አባላት ዲሞክራቲክ መሆን ያልቻለ ድርጅት (ፓርቲ) ለሌሎች ሀገሪቱ ዜጎች እተርፋለሁ ቢል ተአማኒነት ሊኖረው ስለማይችል ድርጅቶችን ስንመረምር ትኩረት የሚያሻው የመጀመሪያ ነጥብ የድርጅቱ ውስጣዊ ዴሞክራሲው ይዘትና ህይወት ይመስለኛል፡» (ገጽ 42)* ይላሉ አቶ ስየ፡፡ አንድነት ፓርቲያችን ውስጥ የታገልነው በሕገ ወጥ መንገድ ተባራችኋል ተብለንና ወደ ግቢ አንዳንደርስ ለፖሊስ አቤት ተብሎብን ፓርቲያችንን ለአንባገነኖች ጥለን አንሄድም በማለት ከአንድ ዓመት በላይ የታገልነው የአንድነትን አመራር ለመጨበጥ የበቁት ወገኖች ከህገ ወጥ ተግባር አንዲታቀቡና በፓርቲው ውስጥ ዴሞክራሲዊ አሰራር አንዲሰፍን ለማድረግ ነበር፡፡ በውስጡ ዴሞክራሲን ያላሰፈነ ፓርቲ መድረክ ውስጥ ቢገባም አይጠቅምም፡ ስለሆነም አንድነትን መድረክ ውስጥ ለማስገባት የምታደርጉትን ግፊት አቁሙና ፓርቲያችንን ለማስተካከል የምናደርገው ትግል በውይይት አልባት አንዲያገኝ « በተዋቂ ግለሰብነትዎና አንድነት አመራሮች ላይ ተጽእኖ ለማሳረፍ የሚችሉ በመሆንዎ» እገዛ ያድርጉ የሚል ጥያቄ ለአቶ ስየ አንዲደርሳቸውም ተደርጎ ነበረ፡፡

የአቶ ስየ ተባባሪነት ግን ህገ ወጥ ድርጊት ከሚፈጽሙት ጋር ሆነ፡፡ ይህም አልበቃቸው እኛን አውጋዥና ኮናኝ ሆኑ፡፡ ይባስ ብለው የአንድነት ምክትል ሊቀመንበር ለመባል በቁ፡፡ አንድ ጥያቄ ላንሳ፡፡ የአንድነት አባልም አመራርም የሆኑት አንድነት ውስጣዊ ዴሞክራሲ የሰፈነበት ፓርቲ ሆኖ አግኝተውት ነው? ለእኛ አልታይ ብሎን ከሆነ «በተባ ብእራቸው» ቢያሳዩን፡፡

አቶ ስየ ቀጠል አድርገው *« አሁን ያለው የፖለቲካ ፓርቲዎች ሁኔታ ከፍ ብሎ ከተጠቀሰው ነጥብ አንፃር ሲታይ ብዙዎቹ ፓርቲዎች የመሪዎቻቸው አንጂ የአባሎቻቸው አይመስሉም፡፡ እንደ ኩባንያ ኃላፊነታቸው የተወሰነ የመሪዎቻቸው የግል ማህበራት ነው የሚመስሉት..፡፡»( ገጽ 42)* የእኛም ትግል አንድነት ወደዚህ ደረጃ አንዳይደርስ ለማድረግ ነበር፡፡ ግን ደረሰ፡፡ ይህን ደግሞ በርሳቸው ትዕዛዝ ኢ/ር ግዛቸውና አቶ አስራት ብቻ የፓርቲውን ፕሮግራም ሲለውጡ ተመልክተ ዋልና ( *ሪፖርተር ጋዜጣ ሚያዝያ 24/2002)* ያረጋገጡ ይመስለኛል፡፡

አሁንም ጥያቄየን ልድገመውና አቶ ስየ ከሚናገሩት በተቀራኒ ቁመና ላይ የሚገኝ ፓርቲ ውስጥ አንደምን ሊገቡ ቻሉ፡፡ አንድነት የጥቂት ግለሰቦች ሳይሆን የአባላቱ አንዲሆን ለማስቻል የታገልነውንስ አንደምን ለማውገዝ በቁ?

☞*« ሀገርን ለመምራት አልመው የሚንቀሳቀሱ ድርጅቶች ውስጣዊ ጉዳያቸው የአባሎቻቸው ጉዳይ ነው በሚል ውስጣቸው ሳይጠራ አሰራራቸውና አካሄዳቸውን ከሀገርና ከሕዝብ ደብቆ መሄዱ ኂላ ኂላ መዘዙ ለመላ ለሀገሪቱ ዜጎች ሁሉ ሊተርፍ የሚችል መሆኑን መገንዘብ ይኖርብናል፡፡» ( ገጽ 44)* በጣም ትክክል ነው፡፡ ግን ምን ያደርጋል አቶ ስየ ጻፉት አንጂ ተግባሪዊነቱ ላይ የሉበትም፡፡

በመጨረሻም *«ሰጥቶ መቀበል መጀመር ያለበት ከቤት ነው» ነው የሚሉት( ገጽ 34)* አቶ ስየ *« ...ከኢሳይያስ ጋር « በሰጥቶ መቀበል» መርህ እደራደራለሁ እያለ የተለየ ሀሳብና አምነት ከያዙት ኢትዮጵያውን ጋር ግን ድርድርና ሰጥቶ መቀበልን አንደ ንትርክና ልማትን አደናቃፊ እንደሆነ ተግባር የሚመለከት መሪ ..»* በማለት ወቀሳ ያቀርባሉ፡፡ ይህንኑ መልሰን *« ከኢህአዴግ ጋር አንደራደር እያለ ደጅ የሚጠና ከራሱ አባላት የእንነጋገር ጥያቄ ሲቀርብለት ወያኔ ያደራጃ ቸው፡ የመንግሥት ድጋፍ ያላቸው፡ ወዘተ የሚል መሪ»..*ብለን አቶ ስየንና ርሳቸውን የሾሙዋቸውን ሰዎች ብንወቅስ አቶ ስዬ ምላሽ ይኖራቸው ይሆን?

ሕገ ወጥነት፡ አንባገነንነት፡ በሥልጣን መባለግ፡ ወዘተ ሌላው ሲፈጽመው አንጂ በራስ ሲፈጸም አይታወቅ ይሆን!!